# ትንሽ ማስታውሻ ለዳኛ ወልደሚካኤል መሸሻ

ከመጋቤ ጥበብ መንገሻ



የቢሸፍቱ ልጅ ነኝ እያለ ሲያታልል፤
ኦሮሞን ካማራው በሐሰት ሲያጋድል፤
ዓለማየሁ ከሶት በማስረጃ ወንጀል፤
በዳኛ ታሰረ በወልደሚካኤል።

በቴዎድሮስ ነበር ወንድነት ጀግንነት፤
በልጁ ዓለማይሁ ተመታ ጠላት፤
በሰራው መትረጌስ በራሱ ጥይት።

የኢትዮጵያ ግዛት ከየመን ምላሽ፤
ያልከው አባቴ ሀገር  ባህረ ነጋሽ፤
ጨካኝ አረምኔ! እናትህን ገድለህ የአባትህ ወራሽ።

የዓለማየሁ እናት ታላቋ እመቤት፤
ያለወለደችው ልጅ እማማ ሲላት፤
አብልታ አሳደጋ  ማርና ወተት፤
ተስፋዮ ጨካኙ «በቡርቃ ዝምታ» በስለት አረዳት።

የሰው ሁሉ ከህደት ሀፍረት የሌለው ነው፤
በትግሬ ተሹሞ ትግሬውን በላው፤
ወርቁን አጠራቅሞ ለናቅፋ ሸጠው።

ታሪክና ጅራት ከበስተኃላ ነው፤
አጥፊያችንን! ተስፋችን ብለን ስንጠራው፤
እናታችን ሲሸጥ ሲያስማማ አገኘነው፤
ጽሎታችን ሰማ ሚካኤል ቀሰፈው።

ስንቱን አጭበርብሮ ያመለጠ ሰው፤
ትንታጉ ዓለማይሁ ተስፋዮን በላው፤
እንዳይነሳ አርጎ አመድ አደረገው።

ዓለማየሁ ከሶት በዳኛ ወለዴ ፊት፤
ተስፋዮ ተገኘ ነገር ሲፈተፍት በሰው ልጅ ሕይወት፤
ወንድሙን በወንድም ሲያስገድል በስለት፡
ብዙም ሳያጠፋት፣ ሳይለበልባት፣ ሳያቃጥላት፤
ሚካኤል ጨበጠው  «በቡርቃ ዝምታ» ያስንሳውን እሳት።

የወንድሞቹን ደም በወንደሙ አፍስሶ፤
እራሱ ምስክር! እራሱ በጻፈው እራሱ ተከሶ፤
ዳኛው ፈረደበት ማስርጃውን ጠቅሶ።

ከሳሽ አለማየሁ ብዙ አስተምሮኛል፤
ለካስዮ አብርሃ በእውነት ተጸጽቷል፤
ሰው በሰውነቱ ከስህተት ይማራል፤
ምጽዋ ወደቡ አሰብም ናፍቆታል፤
ዳኛው ከፈረደ ነገ ይመለሳል፤
ይብላኝ ለተስፋዮ ከሙኑ ይጠጋል።

የቢሸፍቱ ልጅ ነኝ እያለ ሲያምታታ፤
ዝም! ሲል አንበሳው፤ «በቡርቃ ዝምታ»፤
በዘር ተከፋፍሎ ወገኔ ተመታ! ሀገሬ ተፈታ።

እጅህን ስጥ ሲለው እንቢ! አለው አመዴ፤
ያነን ከዳተኛ አታላይ ወንበዴ፤
ቀረ በቢሸፍቱ  ማታላያ  ዘዴ፤
ተስፋዮ ከእንግዲህ አትሆንም ዘመዴ።

ዳኛነት ሲይፍ ነው! ለተመለከተው፤
ከሳሽ ዓለማየሁ የተበደለው ሰው፤
በማስረጃ ይዞ፤ በሄደበት ሂዶ ተከታተለው፤
ሚካኤል በፍርዱ ተስፋዮን ቀሰፈው።

ከቀሳፊ መልአክ ይጠብቀን!
አሜን!

ጥቅምት 2006 ዓ.ም፤  ሎንደን